# በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ መኖረ

## የእግዚአብብሔር መንግስትና ጸሎት

**4፡ ወደ ማን ነው የምንጸልየው? እንዴት ነው የምንጸልየው?**

ይህ ጥያቄ በብዙ ወገኖች ዘንድ ያለ ጥያቄ ነው። ደግሞም በተወሰነ መልኩ ብዙ ወገኖች ግራ የሚጋቡበትና መልስ የሚሹለት ጥያቄም ነው።ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነን እውነት በግልጽ ያስተምረናልና።ይህንንም ቀጥለን እንመልከታለን።

**4:1፡ወደ ማነው የምንጸልየው?** **ጸሎት የሚጸልየው ወደ አብ ነው** ።በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት መሰረት ጸሎት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ነው።በዚህ መቅረብ ውስጥ የጸሎት ተደራሲ ወይም የጸሎታችን አቅጣጫ **ወደ እግዚአብሔር አብ ነው**። ጌታችን ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን እንዴት መጸለይ እንዳለባቸው ባስተማራቸው ጊዜ ያረጋገጠው ይህንን እውነት ነው። :-“እንግዲህ እናንተስ **እንዲህ ጸልዩ** ‘በሰማያት የምትኖር **አባታችን ሆይ፣** ስምህ ይቀደስ” ። ማቴዎስ 6:9

**4፤2፡እንዴት ነው የምንጸልየው?**

**4:2:1 ጸሎት በወልድ (በኢየሱስ ክርስቶስ) ስም ወደ አብ ይቀርባል።**

ጸሎት ወደ አብ መጸለይ እንዳልበት ያስተማርው ጌታችን ኢየሱስ ወደ አብ የምንጸልይውን ጸሎት ደግሞ በስሙ መጸለይ እንዳለብን አስተምሮናል። " **እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና አብም ስለ ወልድ እዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ ማናቸው ንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋልሁ”**። ዮሐ 14:13-14 “ስለዚህም ወደ አብ በኢየሱስ ስም እንጸልያለን”።

**4:2:2** **ጸሎት በመንፈስ ቅዱስ ነው የሚጸለየው።**

አዲስ ኪዳን በስፋት ከሚያስተምራቸው መሰረታዊ ትምህርቶች መካከል መንፈስ ቅዱስ ከአማኝ ጋር ስላለው ግንኙነት የሚናገረው ቀዳሚው ትምህርት ነው። ከዚህ እውነት አንጻር የአማኝን የጸሎት ልምምድ ስንመለከት
ጸሎት በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ/ኀይል እና ምሪት የሚደረግ መንፈሳዊ ልምምድ እንደሆነ እንገነዘባለን።

ይህን እውነት በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።" እንደዚሁም ደግሞ **መንፈስ ድካማችንን ያግዛል** እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና ነገር ግን **መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል"።** ሮሜ 8:26-28 ይሁዳ 20 **"በመንፈ ቅዱስም እየጸለያችሁ...."** ስለዚህ፣ **ጸሎት ሦስቱንም የመለኮት አካላት ያካትታል ማለት ነው።** ይህም ማለት **ወደ አብ ፣በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል** እንጸልያለን ማለት ነው።

**ማጠቃለያ፡ ትክክለኛው የጸሎት መንገድ፡-** ወደ አብ በአክብሮትና በምስጋና በመቅረብ በኢየሱስ ስም መጸልይ ነው፣
ምክንያቱም እርሱ አማላጃችን እና ተስፋችን ነውና።እንዲሁም በሚመራን እና ድካማችንን በሚያግዘው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል መጸልይ ነው**።በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወደ አብ እንጸልያለን።**